# የተግባር ልምምድ / Internship / ፕሮግራም

የኢፌዲሪ መንግስት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ከትውልድ ሀገራቸው ጋር የሚኖራቸው ትስስር የሚጠናከርበት፣ በሀገራቸው ልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸው የሚጎለብትበት፣ መብትና ጥቅማቸውም የሚከበርበት ሁኔታን ለማመቻቸት የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

በዚህም በርካታ የዳያስፖራ አባላት በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ በመሰማራት፣ በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ማሸጋገር፣ ሬሚታንስ ወደ ሀገር ውስጥ በመላክ፣ ንግድና ቱሪዝምን በማስፋፋትና፣ የሀገራችንን ገጽታ በመገንባት ረገድ ተሳትፎ በማድረግ ተጨባጭ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛሉ፡፡ መንግስት እነዚህን መልካም ጅምሮች በማጠናከር ዳያስፖራውን በሀገሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት በማሳተፍ ራሱንና ሀገሩን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የፖሊሲውም አጠቃላይ ዓላማ በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማጠናከር በአገራቸው ልማት፣ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጠንካራ ተሳታፊ ሆነው ራሳቸውን ጠቅመው ትውልድ አገራቸውንም በመጥቀም በጋራ ለማደግ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነም ሰነዱ ያብራራል።

በዚሁ ፖሊሲ ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ግቦች ውስጥ አንዱ በውጭ ሀገራት በሚገኙ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ወጣት ዳያስፖራ አባላት በአገር ውስጥ በሚገኙ የመንግስትና የግል ተቋማት ውስጥ የተግባር ልምምድ /Internship/ የሚያደርጉበትን ፕሮግራም በማመቻቸት ወጣት ዳያስፖራው ከሀገሩ ጋር ያለውን ትስስር ይበልጥ የማጠናከር አሠራር ለመዘረጋት እንደሆነም ተጠቅሷል።

በዚሁ መሠረት የተግባር ልምምድ ፕሮግራም መመሪያ /Internship Programe Directive/ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶና ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

**የመመሪያው ዓላማዎች፡-**

1. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና በሚሲዮኖች የሚካሄዱ የተግባር ልምምድ ፕሮግራሞችን ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ አሠራር የሚካሄድበትን ስርዓት ለመዘርጋት፣
2. በሚኒስቴሩ ዋና መስሪያ ቤት እና በኢትዮጵያ ሚሲዮኖች የሚሰሩ የውጭ አገልግሎት ስራዎችን ተለማማጆች እንዲያውቋቸው ማድረግ እና በሰለጠኑት የሙያ ዘርፍ ባላቸው እውቀት የስራ ዘርፎችን እንዲደግፉ ለማድረግ፣
3. ተለማማጆች የመመረቂያ ጥናቶቻቸው ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ስራ ጋር የሚዛመድ እንዲሆን ለማበረታታት፣

በአጠቃላይ በመንግስት የሚሰጡ ማበረታቻዎች እና የማስፈጸሚያ ስርዓቶችን ዳያስፖራው በየጊዜው በውል ተረድተውና ተገንዝበው እንዲጠቀም ለማስቻል በተለያዩ መንገዶች መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑ ይታወቃል።

በመሆኑም በኖርዲክ አገራት የሚትኖሩና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚትማሩ ወጣት የዳያስፖራ አባላት የፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆን የሚትችሉ መሆኑን እየገለጽን፣ ለበለጠ መረጃ የተግባር ልምምድ ፕሮግራም መመሪያው ከዚህ በታች ቀርቧል።